በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የአምቦ ዩኒቨርስቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የአምቦ ዩኒቨርስቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርስቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የአምቦ ዩኒቨርስቲ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- ✓ የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- ✓ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- ✓ የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- ✓ የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- ✓ የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- ✓ የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) በበጀት ዓመቱ ቀጣይ ከሆኑ እንቅስቃሴዎች የተገኙ ገቢዎች የውስጥ ገቢ መጠን እንዲሁም ገቢውን ለማመንጨት የሚወጣው ወጪ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ ቦርድ መወሰን እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም፤ ከዩኒቨርሲቲው የውስጥ ገቢ የተፈጸመ በአጠቃላይ ድምሩ የብር 1,416,435.00 (444,935.00+971,500.00) ክፍያ በዩኒቨርሲቲው ቦርድ ውሳኔ መሆን ሲገባው በተለያዩ አካላት (በቀድሞ የአምቦ እርሻ ኮሌጅ አካዳሚክ ኮሚሽን እና በዩኒቨርሲቲው የሥራ አመራር) ውሳኔ የተፈጸመ መሆኑ፣
2. በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 8 (ሀ) መሠረት የመንግሥት ገንዘብ ለፀደቀው ዓላማና በተፈቀደው መጠን ብቻ ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም ለ37 ሰዎች ለእንዳንዳቸው ብር

3,000.00፣ በድምሩ ብር 111,000.00 የክብር ክፍያ /honorarium payment/ በሚል በመንግሥት የተፈቀደ ተመን ሳይኖር ከመደበኛ በጀት የተከፈለ መሆኑ፣

3. በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 8 (ሀ) መሠረት የመንግሥት ገንዘብ ለፀደቀው ዓላማና በተፈቀደው መጠን ብቻ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የምግብ አገልግሎት ወደ ገንዘብ እንዲቀየርላቸው ለፈለጉ የዩኒቨርስቲው የክረምት ፕሮግራም ተማሪዎች፣ በሁለት ወር ክፍያ ከመመሪያ ውጭ ብር 46,656.00 (241,056.00-194,400.00) ያላግባብ በብልጫ መከፈሉ፣
4. የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 9/4 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት አስፈላጊ ሲሆን ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸው ባለሙዎች የጽሁፍ ማረጋገጫ መቅረብ እንዳለበት የሚገልጽ ቢሆንም በወሊሶ ካምፓስ አዲስ ለሚዘረጋው የውሃ መስመር ለወሊሶ ከተማ የመጠጥ ዉሀና ፍሳሽ አገ/ጽ/ቤት የተከፈለው የቅድሚያ ክፍያ ብር 190,845.47 በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው አገልግሎቱ ከመገኘቱ እስቀድሞ በወጪ ሂሳብ መደብ 6324 በወጪ የተመዘገበና ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣
5. ሰኔ 2002 በወጣው የግዥ መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15.3 እና 15.4 በአዋጁ እና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልጽ ጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው እና ከግልጽ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 24.12 ላይ የመንግስት መ/ቤቶች በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍለው መግዛት እንደሌለባቸው የተገለጸ ሲሆን ከታህሳስ 12/2008 ጀምሮ ሥራ እንዲውል በተሻሻለው የፌዴራል መንግስት የግዥ መመሪያ አንቀፅ 24.2 መሰረት ደግሞ በፕሮፎርማ የሚገዛ ዕቃ ግዥ ጣሪያ እስከ ብር 200,000.00 እንደሆነ የተገለጸ ቢሆንም፣ በድምሩ የብር 856,535.28 (506,535.80+349,999.48) አንድ ላይ በጨረታ መገዛት የሚችሉት የICT ዕቃዎች ተከፋፍለው የዋጋ ማወዳደሪያ በመሰብሰብ ግዥው የተፈጸመ መሆኑ፣
6. የገቢና የወጪ ሂሳቦች የተያዙትና የተመዘገቡት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር ሥርዓት መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግየዩኒቨርሲቲው የወጪ ሂሳብ ምዝገባ ግንቦት 1999 በወጣው

የፌደራል መንግሥት የሂሳብ አወቃቀር ሥርዓት መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- የቀን ሰራተኞች ምንዳ ብር 97,580.00 በሂሳብ መደብ 6114 መመዝገብ ሲገባው በ6231 የሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑ፤
- ለኦቦንቱ ቤተሰብ አቀፍ ድርጅት ድጋፍ የተሰጠው ብር 150,000.00 በሂሳብ መደብ 6412 መመዝገብ ሲገባው በ6216 የሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑ፣

በድምሩ ብር **247,580.00** የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣

7. ስለ ፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3 አንቀጽ 12 የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ ሊፈጸም ወይም ወጪ ሊያደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም በድምሩ ብር 3,619,201.76 በ2008 በጀት ዓመት ገንዘብ የተከፈለበትና ንብረቱ በ2008 በጀት ገቢ የተደረገ ሆኖ ሳለ በ2009 በጀት ዓመት የወጪ ማስመስከሪያ የተዘጋጀለት እና የተመዘገበ መሆኑ፣
8. እስከበጀት ዓመቱ መጨረሻ መወራረድ ሲገባ ያልተወራረደ ብር 41,568,507.02 (51,576,713.57-1,583,229.93-8,424,976.62) ተሰብሳቢ እና ብር 16,401.00 ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ፣
9. የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደርና አጠቃቀም በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 እና በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003፣ እንዲሁም በፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል በተገለጸው መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ከመደበኛ በጀት ብር 5,522,539.55 እና ከውስጥ ገቢ ወጪ ብር 105,378.18፣ በድምሩ ብር **5,627,917.73** ለሂሳብ መደብ ከተደለደለው በጀት በላይ ሥራ ላይ የዋለ መሆኑ፣

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6 በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች በእኛ አስተያየት የዩኒቨርስቲው የሂሣብ መግለጫዎች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ፣ የተፈፀመውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም።

ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)

1. በፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ክፍል ሦስት አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀፅ 1 ግዥ ፈጻሚ አካላት የሚገዟቸውን ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች ባህሪ የሚያሳይ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት እንዳለባቸው እና ንዑስ አንቀፅ 2 ደግሞ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው የመንግስት መ/ቤቱ ሊገዛ የሚፈልገውን የዕቃ ጥራት፣ ጠቀሜታ፣ ተገቢ ጥንቃቄ፣ እንደ አስፈላጊነቱ መለኪያውን፣ መለያውን፣ መጠሪያውን፣ አስተሻሸጉን፣ ምልክቱን ወይም የአመራረቱን ሂደትና ዘዴውን እንዲሁም ተፈላጊ የሆነውን ባህሪይ የሚያሟላ መሆኑ የሚያረጋግጥበት ሥርዓት የሚገልፅ መሆን እንዳለበት እንዲሁም በፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀፅ 9/2 ማንኛዉም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ዕቃዉ ወይም አገልግሎቱ በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር /Specification/ መሠረት መቅረቡ ወይም አገልግሎት መሰጠቱ፣ የመመሪያው አንቀጽ 9/4 አስፈላጊ ሲሆን ዕቃዉ ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸዉ ባለሙያዎች የፅሁፍ ማረጋገጫ መቅረቡ መረጋገጥ እንደሚገባ የተጠቀሰ ቢሆንም ከሆራይዘን በብር 482,375.14 የተገዛው ጎማ ከአቅራቢዎቹ ሲቀርብ ስለትክክለኛነቱ እና በተጠየቀው ልክና ጥራት ስለመሆኑ የቴክኒክ ኮሚቴ ማረጋገጫ ያልቀረበለት መሆኑ፣
2. የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደርና አጠቃቀም በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 እና በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003፣ እንዲሁም በፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል በተገለጸው መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ከመደበኛ በጀት ብር 39,406,831.26፣ ከካፒታል በጀት ብር 209,066,616.73 እና ከውስጥ ገቢ ወጪ ብር 227,980.65፣ በየሂሳብ መደቡ ከ10% በላይ በድምሩ ብር 248,701,428.64 ያልተሠራበት መሆኑ፤

ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)

- በፌዴራል መንግሥት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 አንቀጽ 8/2 የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል ተገቢው የሙያ ብቃት፤ ዕውቀትና ክህሎት በላቸው ባለሙያዎች

መደራጀት እንዳለበት የተገለጸቢሆንም በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ኦዲት የሰው ኃይል መዋቅር መሠረት ለክፍሉ 14 የኦዲት ባለሙያዎች የሚያስፈልግ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት 2 የኦዲት ባለሙያዎች ብቻ ያሉት በመሆኑ ክፍሉ በባለሙያዎች ያልተሟላ መሆኑ፤፡

- **ንብረት**

አላቂና ቋሚ ዕቃዎች

- በቁጥር ስምንት የሚሆኑ ዘመናዊ የወጥ እና የሻይ ማሽኖች /ድስቶች/ ወደ ዩኒቨርሲቲው ከገቡ ሶስት አመት ያህል ያስቆጠሩ ቢሆንም በኤሌትሪክ ኃይል እጥረት ምክንያት እስከ አሁን ድረስ አገልግሎት ሳይሰጡ ለዝገት እየተጋለጡ መሆኑ፣ ይህ በ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም አስተያየት ተሰጥቶበት የነበረ ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣
- በብዛት 179 የሚሆኑ 5450 DN Brother ሞዴል አዲስ ፕሪንተሮች ወደ የዩኒቨርሲቲው ከገቡ ከ5 ዓመት በላይ የሆናቸው ቢሆንም እስከ አሁን አገልግሎት ሳይሰጡ በእስቶር የተቀመጡ መሆኑ፤
- በበጀት ዓመቱ ዓመታዊ ቋሚ ንብረት ቆጠራ ያልተደረገ በመሆኑ፤

ተሽከርካሪዎች

- አሮጌ እና አዲስ ጎዎች ሳይለያዩ በአንድ መጋዘን ውስጥ የተከማቹ መሆኑ፣
- አገልግሎት ካቆሙ ከሁለት አመት በላይ የሆናቸው እና መወገድ ያለባቸው በርካታ ጎማዎች እና የጎማ ካለመዳሪዎች ያልተወገዱ መሆኑ፤ ይህ በ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም አስተያየት ተሰጥቶበት የነበረ ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣
- አገልግሎት የማይሰጡ የሠሌዳ ቁጥር 4-05500 ኢት 1 ቶዮታ እንዲሁም 4-03971 ኢት እና 4-03973 ኢት፣ ሁለት መካከለኛ አውቶቡሶች መኖራቸው፣

እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች፣

- በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2(በ) መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በውጭ ኦዲት ወይም በውስጥ ኦዲት ሪፖርት በተመለከተው መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡

- በተጨማሪም የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር **982/2008** ክፍል አምስት አንቀጽ 17/3 መሰርት ተመርማሪ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸውና እርምጃ ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የአምቦ ዩኒቨርስቲ የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ውስጥ፣

- ዩኒቨርሲቲው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስተር ሳያስፈቅድ በተማሪዎች ህብረት ስም በተከፈተ ከኢትዮጵ ንግድ ባንክ አምቦ ቅርንጫፍ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000015171786 ከቤቶች ኪራይ፤ ከጀበና ቡና አገልግሎት እና ከፑልና ጁቶኒ አገልግሎት የሚያገኛቸውን ገቢ በራሱ በከፈተ የሂሳብ ቁጥር ገቢ የሚያደርግ መሆኑ፤
- ዩኒቨርሲቲው መዝናና ክበብ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝና ገንዘብ ወጪ ማዘዣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ አምቦ ኮሌጅ የተማሪዎች ማዝናኛ ክበብ ስም በታተመው ክፍያ ቨውቸሮች የሚሰራ መሆኑ፤
- የኒቨርሲቲው 27 ከሚሆኑ የስራ ተቋራጮች በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ሰርቶ ላላስረከቡና ዩኒቨርሲቲውን ላስተጓጎሉበት በድምሩ የብር 8,527,962.55 የጉዳት ካሳ ለመንግስት ገቢ መደረግ ሲገባዉ ያልተደረገ መሆኑን፤
- ዩኒቨርሲቲው በተለያዩ ቀናት የ2ኛ እድገትና ትራንስፎርመሽን እቅድ ላዘጋጁበት ብር 18,000.00፤ ከአምቦ ጉደር አስፓልት ዳር የችግኝ ተከላ አስፈላጊውን ስራ ላከናወኑ ለአስራ አንድ ኮሚቴ አባላት በድምሩ 41,000.00፤ ለካይዘን ስራ ትግበራ የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ የካይዘን ልማት ቡድን አባላት ልዩ ትኩረት ላሳዩ በድምሩ ብር 112,300.00፤ የሪፈራል ሆስፒታል መንገድ በውጪ በኩል ከዋናው አስፓልት መንገድ ጋር የማገናኘት ስራ ላስተባበሩበት ለአስራ ሶስት ኮሚቴ አባላት በድምሩ 34,700.00 ማበረታቻ በሚል አላግባብ ክፍ የተፈጸመ፤
- ዩኒቨርሲቲው በቀን 30/01/08 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 21738 ብር 81,980.73 ወጪ በማድረግ ማገርና ቋሚ እንጨት ግዥ በመፈጸም ለተለያዩ ግለሰቦች ክፍያ

ሲፈጽም ስለ ተከፋይ ተቀናሽ ታክስ መቀነስ የነበረበት ብር 17,278.80 ያልተቀነሰ መሆኑ፤

- በኬሚካል ግምጃ ቤት ውስጥ በግዥና በእርዳታ የተገኙ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ የተለያዩ የኬሚስተሪ መሳሪያዎች እና የተለያዩ ኬሚካሎች ያለአገልግሎት ለብዙ ዓመታት የተቀመጡ መሆናቸውና የመጠቀሚያ ጊዜቸው ያለፈባቸው ኬሚካሎች ሳይወገዱ ለበርካታ ጊዜ የተቀመጡ መሆናቸው፤

የ2007 በጀት ዓመት አዲት ግኝትን በተመለከተ

- የቱሉ ኮርማ የሀገር በቀል ዛፎች ማዕከል ሚያዚያ 26/2007 በተደረገው የርክክብ ስነ ስርዓት ያማረና የደመቀ እንዲሆን ላደረጉ ኮሚቴ አባላት ማበረታቻ እንዲከፈል የዩኒቨርሲቲው ማነጅመንት በሰጠው ውሳኔ መሰረት ብር 73,395.00 አላግባብ የተከፈለው ክፍያ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

በሚሉ ግኝቶች ላይ እስከ 2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ማብቂያ ጊዜ ድረስ እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የአምቦ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የአምቦ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርስቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፤

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርስቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፤

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ፣ያጠቃልላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡ አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በአምቦ ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡ የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የተቋሙ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የአምቦ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. የወጪ ሂሳብ፣

ለተለያዩ አገልግሎቶች የዋለው የወጪ ሂሳብ በፌዴራል መንግስት ታምኖበት በወጡ አዋጆች፤ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱ ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

1.1. በዩኒቨርሲቲው ቦርድ ሳይወሰን ከውስጥ ገቢ የተፈጸመ ወጪ፣

1.1.1 ግኝት

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) በበጀት ዓመቱ ቀጣይ ከሆኑ እንቅስቃሴዎች የተገኙ ገቢዎች የውስጥ ገቢ መጠን እንዲሁም ገቢውን ለማመንጨት የሚወጣው ወጪ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ ቦርድ ይወሰናል ይላል፡፡

በዚህው መሰረት ከዩኒቨርሲቲው የውስጥ ገቢ የተከፈሉ ወጪዎች ትክክለኛነት ከመመሪያው አንጻር ኦዲት ሲደረግ፣

- በቀን 06/10/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 354927 በሂሳብ መደብ 6116 ከተያዘው ብር 339,640.64 ውስጥ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ የተከታታይና ርቀት ትምህርት የ2ኛ እና 4ኛ ዓመት ሚድወይፈር፤ 1ኛ እና 2ኛ ፕራክቲኬም ትርፍ ሰዓት ላስተማሩበት ክፍያ ለ59 ባለሙያዎች ለእያንዳንዳቸው ከብር 288.00 እስከ ብር 15,936.00 በማሰብ በድምሩ የብር 246,060.90 ክፍያ፤ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 1 ተመልክቷል)
- በቀን 21/09/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 355560 በሂሳብ መደብ 6116 በጤና ሳይንስ ኮሌጅ የተከታታይና ርቀት ትምህርት የ3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ዓመት ነርሲንግ ተማሪዎች ፕራክቲሽነሮች በትርፍ ሰዓት ላስተማሩ ለ9 ባለሙያዎች ለእያንዳንዳቸው ከብር 5,973.10 እስከ ብር 34,560.00 በማሰብ በድምሩ የብር 155,669.10 ክፍያ፣ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 2 ተመልክቷል)
- በቀን 25/09/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 355568 በሂሳብ መደብ 6116 የተከታታይና ርቀት ትምህርት ለ229 የአስተዳደር ሰራተኞች ትርፍ ሰዓት ለሰሩበት

ለእያንዳንዳቸው በሰዓት ከብር 60.00 እስከ ብር 900.00 በማሰብ በድምሩ የብር 43,205.00 ክፍያ፣ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 3 ተመልክቷል)

በጠቅላላ ድምሩ የብር 444,935.00 ክፍያ በመመሪያው መሰረት በዩኒቨርሲቲው ቦርድ ውሳኔ መሆን ሲገባው መስከረም 19/1999 ዓ.ም በቁጥር AC/ACM/01/99 በቀድሞ አምቦ እርሻ ኮሌጅ አካዳሚክ ኮሚሽን በተወሰነው መሠረት የተከፈለ መሆኑ፣

- በቀን 30/10/09 በሳጥን ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0888527 ፈተና ለፈተኑ (Examiners) በአንድ ሴሽን ብር 2,500.00 በማሰብ ለ46 ፈታኞች በድምሩ የብር 342,500.00 ክፍያ፤ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 4 ተመልክቷል)
- በቀን 13/10/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 355765 ዩኒቨርሰቲው ከውስጥ ገቢ ሂሳብ **ፈተና** ለፈተኑ (Examiners) በአንድ ሴሽን ብር **2,500** በማሰብ ለ39 ፈታኞች የብር **265,000.00**፤ ለ36 ድህረ ምረቃ አማካሪዎች (Advising) በሚል ለያንዳዳቸው በአንድ ሴሽን ብር 3,500.00 በማሰብ በድምሩ የብር 304,500.00 ክፍያ፤ ለ39 ሊቀመናብርት (Chairpersons) በሚል ለያንዳዳቸው በአንድ ሴሽን ብር 500.00 በማሰብ በድምሩ የብር 59,500.00 ክፍያ፣ በድምሩ የብር 629,000.00 ክፍያ፣ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 5 ተመልክቷል)

በጠቅላላ ድምሩ የብር 971,500.00 (342,500.00 + 629,000.00) ክፍያ በመመሪያው መሰረት በዩኒቨርሲቲው ቦርድ ውሳኔ መሆን ሲገባው ግንቦት 01/2009 ዓ.ም በቁጥር አዩ/ጠ56/44/2009 በዩኒቨርሲቲው የሥራ አመራር በተወሰነው መሰረት የተከፈለ መሆኑን፣

በአጠቃላይ ድምሩ የብር 1,416,435.00 (444,935.00+971,500.00) ክፍያ በቦርዱ ውሳኔ መሆን ሲገባው በተለያዩ አካላት (በቀድሞ የአምቦ እርሻ ኮሌጅ አካዳሚክ ኮሚሽን እና በዩኒቨርሲቲው የሥራ አመራር) ውሳኔ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል።

1.1.2 <u>ሥጋት</u>

- ማናቸውም ክፍያ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ካልተፈጸመ የመንግስት ሀብት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፣ ተጠያቂነትንም ያስከትላል።

1.1.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

- ለወደፊቱ ተመሳሳይ ጉዳይ ሲያጋጥም ክፍያዎቹን መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት መፈጸም ያስፈልጋል።

1.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምለሽ፤</u>

የሥራ አመራሩ፣

- ዩኒቨርሲቲው ከሚሰጣቸው የትምህርት ዓይነቶች አንዱ የሕክምና ትምህርት መሆኑ፣ ሆኖም የሕክምና ትምህርቶች ባብዛኛው የተግባር ትምህርት በመሆኑ የተግባር ትምህርቱን ለመከታተል ህሙማኑ ወዳሉበት ሆስፒታል በመሄድ የተግባር ትምህርቱንእንደሚከታተሉ፣ ትምህርቱን ለመከታተል ወደ ተለያዩ ሆስፒታሎች በሚሄዱበት ወቅት የተግባር ትምህርቱን ለሚያስተምሩ ዶክተሮች ዩኒቨርሲቲው ከሆስፒታሎቹ ጋር የጋራ መግባቢያ ሰነድ ተፈራርሞ ክፍያውን የሚፈጽም መሆኑን፣
- ዩኒቨርሲቲው በተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም ከመጀመሪያ ድግሪ እስከ 2ኛ ድግሪ ትምህርት በተለያዩ ፕሮግራሞች እንደሚሰጥ፣ በመሆኑ ትምህርቱ ፕሮግራም በአከባቢውና በርቀት ያሉ ተማሪዎችን በማስተማር ላይ ቢሆንም የትርፍ ሰዓት ክፍያው በቦርድ ውሳኔ መሆን አለበት የተባለው በቦርድ ለማስጸደቅ ካለፈው የኦዲት አስተያየት በኃላ ኮሚቴ በማቋቋም ጥናት በማድረግ ለማስወሰን ጥናቱን የጨረሱ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ባለው የአከባቢ ጸጥታ ችግር ምክንት የቦርድ አባላቱ ቢሰበሰቡም ያለውን የጊዜውን ችግር መፍትሔ ከመስጠት ባሻገር ሌሎች ሥራዎችን ለመስራትና የቦርድ አባላቱን ለማስወሰን አለመቻሉን ገልጸው በቀጣይ ቦርድ ስብሰባ በሚሰበሰብበት ወቅት ውሳኔ እንዲሰጥ ለማድረግ አስፈላጊውን ጥረት እንደሚያደርጉ በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

1.2 <u>በመንግሥት የወጣ ተመን ሳይኖረው ከመደበኛ በጀት የተፈጸመ ወጪ፣</u>

1.2.1 <u>ግኝት፣</u>

በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 8 (ሀ) መሠረት የመንግሥት ገንዘብ ለፀደቀው ዓላማና በተፈቀደው መጠን ብቻ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በቀን 10/09/09 በሳጥን ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0889698 ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች በመምጣት ለ5ኛ ዙር የምርምር ኮንፍሬንስ ላይ የምርምር ጸሁፋቸውን ላቀረቡት 37 ሰዎች ለእንዳንዳቸው ብር 3,000.00፣ በድምሩ ብር 111,000.00 የክብር ክፍያ /honorarium payment/ በሚል በመንግሥት የተፈቀደ ተመን ሳይኖር ከመደበኛ በጀት የተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡

1.2.2 <u>ስጋት</u>፤

- የመንግስት ገንዘብ አላግባብ ሊባክን ይችላል፡፡
- ክፍያዉ ከመመሪያ ዉጪ ተፈጽሞ ሊሆን ይችላል፡፡

1.2.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፤

- ክፍያዎች ከመፈጸማቸዉ በፊት የክፍያዎቹ ህጋዊነትና አግባቢነት መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ የክፍያዎቹ አስፈላጊነት ከታመነበትም የሚመለከተዉን አካል አስፈቅዶ መሆን ይኖርበታል፡፡

1.2.4 <u>የሥራ አመራሩ ምለሽ</u>፤

የሥራ አመራሩ፣

- ዩኒቨርሲቲው 5ኛ ዙር አገር አቀፍ ኮንፍረንስ ባካሄደበት ወቅት ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት በእንግድነት የተጋበዙ ተመራማሪዎች የምርምር ስራቸውን ያቀረቡና የተገመገሙ ሲሆን እነዚህ ተመራማሪዎች በምርምር ስራቸው አገራችን ከምታካሂደው የለውጥ ስርአት ውስጥ የምርምር ስራዎች ለሀገርቱ ከፍተኛ የለውጥ አቅጣጫ መሰረት በመሆናቸው ላቀረቡት የምርምር ስራ Honorarim የተከፈለ ክፍያ ሲሆን እነዚህ ተመራማሪዎች የተከፈላቸው ደሞዝ እና ጥቅማ ጥቅም ሳይሆን ለሰሩበት የምርምር ስራ በአንድ ጊዜ ብቻ የተከፈለ ሲሆን ከተጠቀሰው መመሪያ ጋር ተያያዥነት የሌለው ክፍያ መሆኑን እንደታወቅልን፡፡

1.2.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>፣

ክፍያው በመንግሥት የወጣ ተመን ስለሌለው ከሚመለከተው የመንግስት አካል ተፈቅዶ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

1.3 <u>በጨረታ መፈጸም ሲገባ ተከፋፍሎ በፐሮፎማ የተፈጸም ግዥ</u>፣

1.3.1 <u>ግኝት</u>፣

ሰኔ 2002 በወጣው የግዥ መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15.3 እና 15.4 በአዋጁ እና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልጽ ጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው እና ከግልጽ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ መመሪያ አንቀጽ

24.12 ላይ የመንግስት መ/ቤቶች በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍለው መግዛት እንደሌለባቸው የተገለጸ ሲሆን ከታህሳስ 12/2008 ጀምሮ ሥራ እንዲውል በተሸሻለው የፌዴራል መንግስት የግዥ መመሪያ አንቀፅ 24.2 መሰረት ደግሞ በፕሮፍርማ የሚገዛ ዕቃ ግዥ ጣሪያ እስከ ብር 200,000.00 እንደሆነ ተገልጿል፡፡

ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው ግዥዎች በአዋጁ እና በመመሪያዉ መሰረት መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፤

- በቀን 27/04/09 በወጪ መመዝገቢያ ቁጥር 06475 የብር 195,115.50፤ በወጪ መመዝገቢያ ቁጥር 06476 የብር 190,502.80 እና በወጪ መመዝገቢያ ቁጥር 06471 የብር 120,917.50፣ በድምሩ የብር 506,535.80 ለICT ክፍል የሚያገለግሉ ዕቃዎች፣
- በቀን 28/07/09 በወጪ መመዝገቢያ ቁጥር 09856 የብር 199,999.78 እና በወጪ መመዝገቢያ ቁጥር 09875 የብር 149,999.70፣ በድምሩ የብር 349,999.48 ለICT ክፍል የሚያገለግሉ ዕቃዎች፣

በድምሩ የብር 856,535.28 (506,535.80+349,999.48) አንድ ላይ በጨረታ መገዛት የሚችሉት የICT ዕቃዎች ተከፋፍለው የዋጋ ማወዳደሪያ በመሰብሰብ ግዥው የተፈጸመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

1.3.2 ስጋት፣

- አስፈላጊነታቸው በመንግስት ታምኖበት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን መተላለፍ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- አሠራሩ መንግስት ከጥቅል ግዥ ሊያገኝ የሚችለውን ጥቅም ያሳጣዋል፡፡
- መመሪያን ያልተከተለ የግዥ ሥርዓት ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

1.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ዩኒቨርሲቲው የሚፈፅማቸው በግልጽ ጨረታ በጥቅል ሊገዙ የሚችሉትን ግዥዎች በእቅድ ይዞ በመመሪያው መሠረት እንዲገዙ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ለወደፊቱም የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ተገቢው ጥንቃቄ ሊያደረግ ይገባል፡፡

1.3.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ በፕሮፎርማ የተከናወኑት ዕቃዎች የICT ሲሆኑ ይሄው ለተማሪዎች ዶርምና ቤተመፅሐፍት የWifi እና በቂ መፅሐፍት ባለመኖሩ E-Book ማግኘት እንዲችሉ

የእነዚህ infrastructure ሥራ ለመሥራት የተገዙ ዕቃዎች በመሆኑ እና እነዚህን ዕቃዎች በጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ጊዜ የሚወስድና በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ችግር የሚፈጥር በመሆኑ ግዥው በፕሪፎርማ የተከናወነ ቢሆንም ለወደፊት ማንኛውም ግዥ በእቅድ ውስጥ ተካቶ በተቻለ መጠን በጨረታ እንዲገዛ እንደሚያደርጉ በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

1.4 በብልጫ የተከፈለ የተማሪዎች ምግብ ሂሳብ፣

1.4.1 ግኝት

በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 8 (ሀ) መሠረት የመንግሥት ገንዘብ ለፀደቀው ዓላማና በተፈቀደው መጠን ብቻ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የምግብ አገልግሎት ወደ ገንዘብ እንዲቀየርላቸው ለፈለጉ የዩኒቨርስቲው የክረምት ፕሮግራም ተማሪዎች፣

- በቀን 28/11/08 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 353085 የሀምሌ/08 እና የነሐሴ/08 የምግብ ወጪያቸው በመንግስት የተሸፈነ ተማሪዎች መንግስት በተመነው ለአንድ ተማሪ ብር 15.00 ሂሳብ፣ ለ216 ተማሪዎች ብር 194,400.00 (ብር 15*30 ቀን *216 ተማሪ * 2 ወር) መክፈል ሲገባ ብር 3.60 ጭማሪ በማድረግና ብር 18.6 በማሰብ ብር 241,056.00 (ብር 18.60*30 ቀን * 216 ተማሪ*2 ወር) በመክፈሉ በሁለት ወር ክፍያ ከመመሪያ ውጭ ብር 46,656.00 (241,056.00-194,400.00) ያላግባብ በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

1.4.2 ሥጋት

- ክፍያዎችን በፋይናንስ አዋጅ፣ ደንብና መመርያ መሰረት እና ለተሰጠው አገልግሎት ብቻ አለመፈጸም የመንግስትን ሀብት ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

1.4.3 የማሻሻያ ሀሳብ

- ማንኛውም ክፍያ ደንብና መመሪያን መሰረት አድረጎ መከናወን አለበት፡፡ ስለሆነም ያለአግባብ በወጪ የተመዘገበው ክፍያ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ተማሪዎቹ አድራሻቸው ተፈልጎ ገንዘቡን እንዲመልሱ ሊደረግ ይገባል፡፡

1.4.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፣

የሥራ አመራሩ በብልጫ የተከፈለ የተማሪዎች የምግብ ክፍያ የክፍያ ስሌት የ62 ቀናት የ363 ተማሪዎች በቀን 15 ብር ማለትም ብር 337,590.00 መከፈል ሲኖርበት በስህተት

የመኝታ ተጨምሮ የ62 ቀን ለ363 ተማሪዎች ብር 405,108.00 ወጪ ሆኖ የተከፈለ ሲሆን (405,108.00-337,590.00=67,518.00) በወቅቱ የሂሳብ ስሌት ላይ ስህተት መኖሩን ከኦዲቱ ግኝት በኋላ የተረዳን ሲሆን በአሁኑ ወቅት በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በቀጣይ ትምህርታቸውን ሊከታተሉ ከመጡ ተማሪዎች ውስጥ ብር 27,343.00 ተመላሽ ያደረግን መሆኑን እየገለጽን ገቢ የተደረገበትን PV/RV ያያዝን ሲሆን ቀሪ ብር 40,175.00 ሲሆን ቀሪዎቹ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ያጠናቀቁና የተመረቁ በመሆናቸው ኦርጅናል የትምህርት ማስረጃ ለመውሰድ በሚመጡበት ወቅት ተመላሽ እንዲያደርጉ ጥረት ከማድረግ ውጪ ተማሪዎቹ ከተለያዩ ቦታዎች መጥተው ትምህርታቸውን ስለሚከታተሉ በቀላሉ አድራሻቸውን ለማወቅ የሚያስቸግር መሆኑን እየገለጽን በብልጫ የተከፈለውን ገንዘብ በማስመለስ ሂደት ዩኒቨርሲቲው ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር በመሆን የተቻለውን ጥረት የሚያደርግ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

1.4.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት፣</u>

ግኝቱ አስቀድሞ ሲያዝ የ364 ተማሪዎች በ60 ቀናት ብር 406,224.00 ሲሆን ብር 27,528.00 ከ148 ተማሪዎች በደረሰኝ ቁጥር 355691 ተመላሽ ለመደረጉ ለኦዲት ማስታወሻ በተሰጠ ምላሽ ስለተገለጸ ይህ ተቀንሶ ግኝቱ በ216 ሰዎች ብቻ የተያዘ መሆኑ ታውቆ ያልተተካው ሂሳብ እንዲተካ ክትትል መደረግ አለበት፡፡

1.5 <u>በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ክፍያ፣</u>

1.5.1 <u>ግኝት</u>

ስለ ፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3 አንቀጽ 12 የመንግሥት ገንዘብ ክፍያ ሊፈጸም ወይም ወጪ ሊያደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ መሆኑን ይገልጻል፡፡

በዚሁ መሰረት የዩኒቨርሲቲው ክፍያዎችና ግዥዎች በጀት ዓመታቸውን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- የብር 2,780,595.23 የማገዶ እንጨት ከሀዳስ በርሄ የእህል ንግድ ድርጅት በቀን 16/10/2008 ገንዘቡ ተከፍሎ በቀን 15/10/08 (2008 በጀት ዓመት) ዓ.ም ንብረቱ ገቢ የተደረገ ቢሆንም ሂሳቡ ከበጀት ዓመቱ ውጭ በ2009 በጀት ዓመት በቀን 26/11/08 (በ2009 በጀት ዓመት) በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 353818 በሂሳብ መደብ 6216 በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፣

- የብር 838,606.53 የተማሪዎች ምግብ ለወሊሶ ካምፓስ ከሀዳስ በርሄ የእህል ንግድ ድርጅት በቀን 21/10/2008 ገንዘቡ ተከፍሎ በቀን 17/10/08 ዓ.ም (2008 በጀት ዓመት) ንብረቱ ገቢ የተደረገ ቢሆንም ሂሳቡ በቀን 26/11/08 (በ2009 በጀት ዓመት) በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 353819 በሂሳብ መደብ 6216 በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፣

በድምሩ ብር 3,619,201.76 በ2008 በጀት ዓመት ገንዘብ የተከፈለበትና ንብረቱ በ2008 በጀት ገቢ የተደረገ ሆኖ ሳለ በ2009 በጀት ዓመት የወጪ ማስመስከሪያ የተዘጋጀለት እና የተመዘገበ መሆኑ ተረጋግጧል።

1.5.2 <u>ሥጋት</u>

- ደንብና መመሪያ ተፈጻሚ እንዳይሆን ከማድረጉ በተጨማሪ ያለፈውን በጀት የወጪ ሂሳብ ዝቅ እንዲልና የ2009 በጀት ዓመቱ ከፍ እንዲል ሊያደርገው ይችላል።

1.5.3 **<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>**

- ክፍያ በአዋጁ መሠረት የበጀት ዓመቱን ጠብቆ ሊከናወን ይገባል።

1.5.4 **<u>የሥራ አመራሩ ምለሽ፤</u>**

የሥራ አመራሩ ዩኒቨርሲቲው ጨረታ በሚያወጣበት ወቅት የክረምት ተማሪዎችን ታሳቢ በማድረግ እስከ ነሐሴ 30/2008 በመሆኑ እና ገቢ የሆኑት አቅርቦቶች አገልግሎት ላይ የዋሉት በ2009 ዓ.ም የበጀት ወቅት ላይ ስለሆነ ምንም እንኳን ንብረቱ ገቢ ቢደረግም ክፍያው በወቅቱ ያልተፈፀመ መሆኑን ገልጸው በቀጣይ ይህንን አስመልክቶ ገቢ የሚሆኑትን አቅርቦቶች የበጀት ጊዜያቸውን የጠበቀ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ክትትል እንደሚደርጉ በምላሻቸው ገልጸዋል።

1.6 **<u>የቴክኒክ ኮሚቴ ማረጋገጫ ያልቀረበለት ግዥ፤</u>**

1.6.1 **<u>ግኝት</u>**

የፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ክፍል ሦስት አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀፅ 1 ግዥ ፈጻሚ አካላት የሚገዟቸውን ዕቃዎች፣ የግንባታ ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች ባህሪ የሚያሳይ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ ማዘጋጀት እንዳለባቸው እና ንዑስ አንቀፅ 2 ደግሞ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫው የመንግስት መ/ቤቱ ሊገዛ የሚፈልገውን የዕቃ ጥራት፣ ጠቀሜታ፣ ተገቢ ጥንቃቄ፣ እንደ አስፈላጊነቱ መለኪያውን፣ መለያውን፣ መጠሪያውን፣ አስተሻሸጉን፣ ምልክቱን ወይም የአመራረቱን

ሂደትና ዘዴውን እንዲሁም ተፈላጊ የሆነውን ባህሪይ የሚያሟላ መሆኑ የሚያረጋግጥበት ሥርዓት የሚገልፅ መሆን አለበት ይላል፡፡

የፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀፅ 9/2 ደግሞ ማንኛዉም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ዕቃዉ ወይም አገልግሎቱ በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር /Specification/ መሠረት መቅረቡ ወይም አገልግሎት መሰጠቱ፣ የመመሪያው አንቀጽ 9/4 አስፈላጊ ሲሆን ዕቃዉ ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸዉ ባለሙያዎች የፅሁፍ ማረጋገጫ መቅረቡ መረጋገጥ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡

በዚህ መሰረት ማናቸውም ግዥ ከተከናወነ በኋላ ንብረቱ ገቢ ሲሆን በሚመለከተው ቴክኒክ ከሚቴ መረጋገጡን ለመረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ04/08/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 05593 ከሆራይዘን በብር 482,375.14 የተገዛው ጎማ ከአቅራቢዎቹ ሲቀርብ ስለትክክለኛነቱ እና በተጠየቀው ልክና ጥራት ስለመሆኑ የቴክኒክ ኮሚቴ ማረጋገጫ ያልቀረበለት መሆኑ ታውቋል፡፡

1.6.2 <u>ሥጋት</u>

- በግዥ የሚመጣ ዕቃ በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት በቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ የሚገባ ከሆነ የመንግስት ሀብት ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡
- ጥራት የሌላቸው ዕቃዎችን በመረከብ ዕቃዎቹ ማገልገል ለሚገባቸው ጊዜ አገልግሎት ላይሰጡና ለብልሽት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡

1.6.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

- ለወደፊት ዩኒቨርሲቲው ማናቸውንም የዕቃ ግዥ ሲያከናውን ዕቃው በናሙናው መሰረት ስለመግባቱ በቴክኒክ ኮሚቴ ሊረጋገጥ ይገባል ፡፡

1.6.4 <u>የሥራ አመራሩ ምለሽ፤</u>

የሥራ አመራሩ የሆራይዘን ጎማ የተገዛው የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት አሸናፊነቱን ከላከው ድርጅት በመሆኑ የጠያቂው ክፍል የትራንስፖርትና ጥገና ቡድን መሪ የሆኑ አቶ አለማየሁ ሆርዶፋ እና የዕቃ ግዥ ሰራተኛ ጒማው በግዥ ጥያቄው ላይ በተጠየቀው ልክና መጠን ስለመሆኑ እንዲሁም የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት አሸናፊውን ለይቶ በላከው Specifcation መሰረት ስለመሆኑ በቦታው በመገኘት በማረጋገጥ ግዥ የተፈፀመ መሆኑን በምለሻቸው ገልጸዋል፡፡

1.6.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>፣

ለወደፊቱ የሚገዛ ዕቃ በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር /Specification/ መሠረት ለመሆኑ በጠያቂው ክፍል ሳይሆን ገለልተኛ ሆኖ በተቋቋመ ኮሚቴ መረጋገጥ አለበት፡፡

1.7 <u>በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ</u>

1.7.1 <u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 9/4 ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት አስፈላጊ ሲሆን ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸው ባለሙዎች የጽሁፍ ማረጋገጫ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡

ክፍያዎች በዚሁ መሰረት መፈጸማቸውን ለማረጋገት አዲት ሲደረግ፣ ዩኒቨርሲቲው በወሊሶ ካምፓስ አዲስ ለሚዘረጋው የውሃ መስመር ከወሊሶ ከተማ የመጠጥ ዉሀና ፍሳሽ አገ/ጽ/ቤት ጋር በተዋዋለው መሰረት በ24/09/2009 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 18897 የተከፈለው የቅድሚያ ክፍያ ብር 190,845.47 በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው አገልግሎቱ ከመገኘቱ እስቀድሞ በወጪ ሂሳብ መደብ 6324 በወጪ የተመዘገበና ሪፖርት የተደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

1.7.2 <u>ሥጋት</u>

- የተፈለገው አገልግሎት በትክክል በጥራትና በጊዜ ላይገኝ ይችላል፡፡
- ያለአግባብ ተሰብሳቢን ዝቅ እና ወጪን ከፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡

1.7.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

- ክፍያዎች በወጪ ከመያዛቸው በፊት የተረከብነው ዕቃ ወይም ያገኘነውን አገልግሎት ስለመኖሩ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
- ለወደፊቱም የቅድሚያ ክፍያ ምዝገባ በወጪ ሂሳብ መያዝ እንደሌለበት ታውቆ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.7.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፤

የሥራ አመራሩ በወጪ የተመዘገበ ቅድሚያ ክፍያ በ2009 በጀት ዓመት በአምቦ ዩኒቨርሲቲ ወሊሶ ካምፓስ የውሃ መስመር ዝርጋታ የወሊሶ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ለስራው የሚያስፈልገውን ወጪ ዝርዝር በማውጣት ሥራው ከመጀመሩ አስቀድሞ ክፍያው እንዲፈፀም በተጠየቀት መሠረት ክፍያውን የፈፀሙ ሲሆን ስራው ወዲያው

ተጠናቆ አገልግሎቱን ዩኒቨርሲቲው ያገኘ መሆኑን ጠቅሰው ክፍያው በወጪ ተመዝግቦ የተያዘው አገልግሎቱን ወዲያው ዩኒቨርሲቲው እንደሚያገኝና ወደቀጣይ በጀት የማይዞር አፋጣኝ ሥራ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንደሆነ በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

1.7.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>፣

አገልግሎቱ ለመገኘቱ በምላሹ የተገለጸ ቢሆንም ለወደፊቱ የግዥ ቅድሚያ ክፍያ ዕቃው እስኪገባ ወይም አገልግሎቱ እስኪገኝ በወጪ መመዝገብ እንደሌለበት ታውቆ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

1.8 <u>የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ወጪ</u>፣

1.8.1 <u>ግኝት</u>

የዩኒቨርሲቲው የወጪ ሂሳብ ምዝገባ ግንቦት 1999 በወጣው የፌደራል መንግሥት የሂሳብ አወቃቀር ሥርዓት መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በቀን 18/08/09 በጥሬ ገንዘብ ክፍያ ቁጥር 0889136 ለቀን ሰራተኞች ምንዳ የተከፈለው ብር 97,580.00 በሂሳብ መደብ 6114 መመዝገብ ሲገባው በ6231 የሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑ፤
- በቀን 29/10/09 በወጪ መስመስከሪያ ቁጥር 355572 ለኦቦንቱ ቤተሰብ አቀፍ ድርጅት ድጋፍ የተሰጠው ብር 150,000.00 በሂሳብ መደብ 6412 መመዝገብ ሲገባው በ6216 የሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑ፣

በድምሩ ብር **247,580.00** የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

1.8.2 <u>ሥጋት</u>

- ወጪዎች በተገቢው የወጪ ሂሳብ መደብ ተመዝግበው ሪፖርት ካልተደረጉ የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም የሂሳብ አያያዙ በበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡

1.8.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

- የወጪዎች ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ትክክለኛ የወጪ ሂሳብ አርዕስታቸውን የጠበቁ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ከበጀት አርእስታቸው ውጭ የተመዘገቡ የወጪ ሂሳቦችም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጋር በመመካከር ማስተካከያ ሊሰራላቸው ይገባል፡፡

1.8.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ፣

- ሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ምዝገባ ሰነዱ በሚዘጋጅበት ወቅት በወጪ ማስመስከሪያ /PV/ ላይ በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ላይ የተገለፀ ሲሆን ነገር ግን ወደ አይቤክስ በሚመዝገብበት ጊዜ የተፈጠረ ስህተት በመሆኑ ለወደፊቱ ጥብቅ ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን፣ (ለ6231/6114)
- ብር 150,000.00 ለአቦንቱ ለድርጅት ደጋፊ የሚለው ሰነድ ሲዘጋጅ በወጪ ማስመስከሪያ ላይ በትክክለኛ ኮድ ተመዝግቦ ወደ አይቤክስ በሚመዝገብበት ወቅት በምዝገባ ስህተት 6216 ተብሎ የተመዘገበ ሲሆን ለወደፊቱ እንደዚህ አይነት ስህተት እንዳይደረገም የሚጠነቀቁ መሆኑን፣ ለሥራ አመራር ደብዳቤ በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

2. ተሰብሳቢ ሂሳብ፣

2.1 ግኝት፣

- የፌዴራል መንግስት ፋይናንስ አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 የቅድሚያ ክፍያ በተሰጠው በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ መወራረድ አለበት ይላል፡፡
- በፌዴራል መንግስት ሂሳብ አያያዝ እና አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 የሂሳብ አያያዝ አፈፃፀም ንዑስ ቁጥር 4 ተሰብሳቢ ሂሳብ (መ) ደግሞ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሰብ መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ይገልፃል፡፡

ይሁን እንጅ በዩኒቨርሲቲው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በድምሩ ብር **51,576,713.57** በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ የነበረ ሲሆን ይህም፣

- በሂሳብ መደብ 4201 ከተመለከተው ሂሳብ ውሰጥ ብር 30,199.59 **ውዝፍ** ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሆኖ ከዚህ ውስጥ ብር 6,323.59 ከትምህርት ሚ/ር የሚፈለግ እና የቆይታ ጊዜው የማይታወቅ ሲሆን ቀሪው ብር 23,876.00 በተለያዩ 10 የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች ስም የተያዘና ከ2006 ሰኔ 30/2009 ድረስ ሳወራረድ የቆየ መሆኑ፤ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 6 ተመልክቷል፡፡)

- ልዩ ልዩ ተሰብሳቢ በሂሳብ መደብ 4210 የተያዘው ብር 28,609,958.49 በአምቦ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ስም ያለና አብዛኛው ከሶስት ዓመት በላይ የቆየ መሆኑ፤
- በዕቃ አቅርቦት የቅድሚያ ክፍያ /ሂሳብ መደብ 4253/ ከተያዘው ሂሳብ ውስጥ ብር 22,936,555.49 ከአንድ እስከ አራት ዓመት የቆየ ሲሆን በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ የዕቃና አገልግሎት አቅርቦት የቅድሚያ ክፍያ ለዕቃና አገልግሎት አቅራቢ ግለሰብ፣ ድርጅትና የመንግሥት ተቋም የተሰጠ ቢሆንም እስከ ሰኔ 30/2009 ድረስ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 7 ተመልክቷል።)

ተረጋግጧል።

2.2 ሥጋት፣

- ሂሳቡ በወቅቱ ካልተወራረደ የመንግስት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ባክኖ ሊቀር የሚችልበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል። በተጨማሪም በሂሳብ መግለጫው ላይ በየዓመቱ በተደጋጋሚ እንዲታይ ከማድረጉም ሌላ የዩኒቨርሲቲው በጀት አላግባብ እንዲቀነስ ያደርገዋል።

2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ያልተወራረደው ሂሳብ በሚመለከታቸው አካላት እንዲወራረድ ሆኖ ለወደፊቱ የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል።

2.4 በሚመለከተው የሥራ ክፍል የተሰጠ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ፣

- በሂሳብ መደብ 4201 ከተያዘው ተሰብሳቢ ውስጥ ከት/ሚኒስቴር የሚሰበሰብ ተብሎ ከ20 ዓመት በላይ በሰነድነት ብር 6,323.59 የተያዘ ሲሆን ሌሎቹ ብር 16,676.00 ለዩኒቨርሲቲው ሥራ በሰነድ ከወጡ በኋላ መልቀቂያ ሳይጠይቁ ዩኒቨርሲቲው የለቀቁ ሲሆን ብር 7,200.00 ለሥራ ጉዳይ በሰነድ ካወጡ በኋላ በድንገተኛ አደጋ በሞት የተለዩ መሆናቸውን፣
- በሂሳብ መደብ 4210 ለአዋሮ ካምፓስ የተለያዩ ኮንስትራክሽን ሥራ የሚሰራው ቀደም ሲል ት/ሚኒስቴር ያሰራ የነበረውን በቤቶች ልማት ክትትል የነበረው በአሁኑ ወቅት ዩኒቨርሲቲው ተረክቦ የሚያሰራ በመሆኑ የግንባታ ውል በሚደረግበት ወቅት ሲሚንቶውን ዩኒቨርሲቲው ገዝቶ የሚያቀርብ ሲሆን በአካባቢው ፀጥታ ችግር ምክንያት

ግንባታው በመዘግየቱና በመጓጓዣ እጥረት መክንያትም እቃው ሙሉ በሙሉ ገቢ ያልሆነ በመሆኑ ሳይወረረድ የዘገየ ሲሆን በአሁኑ ወቅት እየተጓጓዘ ስለሆነ በአጭር ጊዜ ተወራርዶ የሚጠናቀቅ መሆኑን፣

- የ4253 የተለያዩ ዕቃ አቅራቢዎች የመንግሥትና የግል ድርጅቶች ከዩኒቨርሲቲው ጋር ውል በመዋዋል የቅድሚያ ክፍያ ከወሰዱ በኃላ የተጫረቱትን ዕቃ ባለማቅረባቸው በቅድሚያ የወሰዱት በተሰብሳቢነት እየታየ እንደሚገኝ፣ ሆኖም ዩኒቨርሲቲው፡-
  - ➢ ሲማን ቢዝነስ ትሬዲንግን በመክሰስ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው የፍርድ አጻጸም በወጠየቁ ምክንያት ገቢ ያልተደረገ በመሆኑ እንጂ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ እንዲያደርግ በፍርዱ ቤት የተወሰነ መሆኑን (የውሳኔው ኮፒ ከምላሹ ገር የመጣ፣
  - ➢ ከግዥ ኤጀንሲ የመፅሐፍት ግዥ ወደ 8,424,976.62/ ስምንት ሚሊዮን አራት መቶ ሃያ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስባ ስድስት ብር ከ62/100 ሣንቲም/ መፅሐፉን ገቢ አድርገው ሞዴል 19 ያስቀረጡ ሲሆን ደረሰኝ ባለማቅረባቸው ምክንያት በተሰብሳቢነት ሊታይ መቻሉን፣
  - ➢ ሜዲካል ፈንድ ሰፕላይስ የህክምና ዕቃ አቅርቦት ወደ 1,895,599.93 /አንድ ሚሊዬን ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ብር ከ93/100 ሣንቲም/ ገቢ አድርገው ሞዴል 19 የተቀረጠ መሆኑን፣
  - ➢ ቀሪዎቹንም አቅራቢዎች ዩኒቨርሲቲው ለየድርጅቶቹ በያድራሻቸው ደብዳቤ የፃፈ ሲሆን አቅራቢዎቹ በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ በሕግ ተጠያቂ የሚያደርጋቸው መሆኑን የገለጸላቸው መሆኑን፣

ለሥራ አመራር ደብዳቤ በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

2.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>፣

- በሂሳብ መደብ 4201 የተያዘውን ሂሳብ በተመለከተ ክትትል ተደርጎበት መሰብሰብ/ማወራረድ የሚቻለውን መሰብሰብ/ማወራረድ የሚገባ ሲሆን መሰብሰብ/ማወራረድ በማያቻለው ላይ ደግሞ በመመሪያው መሠረት እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡
- በሂሳብ መደብ 4253 ከተያዘው ደግሞ፡-
  - ➢ በሲማን ቢዝነስ ትሬዲንግ የተያዘው ለዩኒቨርሲቲው የተወነና የውሳኔው ፎቶ ኮፒ ከምላሹ ጋር የቀረበ ቢሆንም እሰከ ውሳኔው አፈጻጸም ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡

- ከመድኃኒት ፈንድ የሚፈለገው አስቀድሞ በተሰብሳቢ የተያዘው ብር 2,435,688.00 ሲሆን መድሃኒቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ (ሞዴል 19) የቀረበው ለብር 1,583,229.93 በመሆኑ በቀሪው ብር 852,458.07 (2,435,688.00-1,583,229.93) ላይ ክትትል መደረግ አለበት።
- በግዥ ኤጀንሲ ስም ተይዞ የነበረው ደግሞ ብር 15,750,000.00 በመሆኑ ቀሪው ብር 7,325,023.38 (15,750,000.00-8,424,976.62) መወራረድ አለበት።

3. ተከፋይ ሂሳብ፣

3.1 ግኝት፣

የዩኒቨርስቲው ተከፋይ ሂሳብ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሒሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በሂሳብ መደብ 5028 /በመንግሥት መ/ቤት ልዩ ልዩ ተከፋዮች/ የተያዘው ብር **16,401.00** በተለያዩ ግለሰቦች ስም ያለ ሲሆን ከአንድ እስከ ሶስት ዓመት በላይ እየተንከባለለ የመጣና እስከ ሰኔ 30/2009 ድረስ ያልተወራረደ መሆኑ ታውቋል።

3.2 ሥጋት፣

- የተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ካልተወራረደ ወይም ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ ሪፖርቱን ተአማኒነት ሊያሳጣው ይችላል።

3.3 የማሻያ ሀሳብ፣

- ተከፋይ ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት በወቅቱ ለሚመለከተው አካል መከፈል ይኖርባቸዋል። ይህ የማይሆን ከሆነ ግን የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል።

3.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ በሂሳብ መደብ 5028 ተመዝግቦ የሚገኙ ተከፋዮች ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ጨረታዎች በሚያወጣበት ወቅት ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙ ተጫራቶች ቀርበው እንዲመለስላቸው ስላልጠየቁና ዩኒቨርሲቲውም ግለሰቦችን ለማፈላለግ ገቢ በሚያደርጉበት ወቅት ምንም አይነት አድረሻ ስለሌላቸው ተመላሽ ለማድረግ የተቸገረ እና ተከፋይ ከአመት ወደ አመት እየተንከበላለ የመጣ መሆኑን በምላሻቸው ገልጸዋል።

3.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ጋር በመመካከር ለሂሳቡ መፍትሄ ሊፈለግ ይገባል።

4. የበጀት ሂሳብ፣

4.1 ግኝት፣

- የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደርና አጠቃቀም በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 እና በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003፣ እንዲሁም በፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል በተገለጸው መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

ከመደበኛ በጀት ከበጀት በላይ የወጣ				
የሂሳብ መደብ	**የተስተካከለ በጀት**	**ሥራ ላይ የዋለ**	**ከበጀት በላይ የወጣ**	**በመቶኛ**
6216	77,350,540.00	82,638538.90	5,297,998.90	7
6258	6,490,000.00	6,685,384.94	195,384.94	3
6412	9,000,000.00	9,029,155.71	29,155.71	0.323
ድምር	**92,840,540**	**98,353,079.55**	**5,522,539.55**	6
ከመደበኛ በጀት ያልተሰራበት በጀት				
የሂሳብ መደብ	**የተስተካከለ በጀት**	**ሥራ ላይ የዋለ**	**ያልተሰራበት**	**በመቶኛ**
6133	62,780.00	27,711.42	35,068.58	56%
6211	8,570,220.00	4,782,048.63	3,788,171.37	44%
6212	8,850,000.00	7,954,783.34	895,216.66	10.11%
6213	5,250,000.00	1,321,150.34	3,928,849.66	75%
6214	15,010,000.00	4,193,207.84	10,816,792.16	72%
6215	7,350,000.00	2,700,591.81	4,649,408.19	63%
6218	4,950,000.00	4,116,071.98	833,928.02	17%
6219	5,000,000.00	3,328,506.06	1,671,493.94	33%
6221	1,000,000.00	309,284.02	690,715.98	69%

6222	800,000.00	62,115.74	737,884.26	92%
6223	6,550,000.00	5,564,547.63	985,452.37	15%
6232	2,610,000.00	1,850,224.29	759,775.71	29%
6243	300,000.00	259,757.16	40,242.84	13%
6251	3,896,340.00	1,136,415.72	2,759,924.28	71%
6252	420,000.00	10,274.35	409,725.65	98%
6254	1,500,000.00	1,305,202.72	194,797.28	13%
6256	1,300,000.00	560,655.73	739,344.27	57%
6257	1,500,000.00	913,783.44	586,216.56	39%
6271	10,158,910.00	6,476,642.34	3,682,267.66	36%
6417	1,000,000.00	556,843.43	443,156.57	44%
6419	1,552,930.00	794,530.75	758,399.25	49%
ድምር	**87,631,180.00**	**48,224,348.74**	**39,406,831.26**	
ከካፒታል በጀት ያልተሠራበት በጀት				
6313	64,215,400.00	51,308,455.02	12,906,944.98	20%
6314	500,000.00	135,700.00	364,300.00	73%
6321	1,700,000.00	-	1,700,000.00	100%
6323	271,276,000.00	140,695,614.77	130,580,385.23	48%
6324	106,629,000.00	43,114,013.48	63,514,986.52	60%
ድምር	**444,320,400.00**	**235,253,783.27**	**209,066,616.73**	
ከውስጥ ገቢ ከበጀት በላይ የወጣ				
የሂሳብ መደብ	**የተስተካከለ በጀት**	**ሥራ ላይ የዋለ**	**ከበጀት በላይ የወጣ**	**በመቶኛ**
6116	19,083,550.00	19,179,061.88	95,511.88	1%
6231	250,000.00	257,829.30	7,829.30	3%
6232	31,000.00	33,037.00	2,037.00	7%
ድምር	**19,364,550**	**19,469,928.18**	**105,378.18**	

ከውስጥ ገቢ ያልተሠራበት በጀት				
የሂሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	ሥራ ላይ የዋለ	ሥራ ላይ ያልዋለ	በመቶኛ
6216	1,240,950.00	1,014,601.35	226,348.65	18%
6233	3,000.00	2,268.00	732.00	24%
6255	6,800.00	5,900.00	900.00	13%
ድምር	**1,250,750.00**	**1,022,769.35**	**227,980.65**	

- ከመደበኛ በጀት ብር 39,406,831.26፣ ከካፒታል በጀት ብር 209,066,616.73 እና ከውስጥ ገቢ ወጪ ብር 227,980.65፣ በየሂሳብ መደቡ ከ10% በላይ በድምሩ ብር **248,701,428.64** ያልተሠራበት መሆኑ፤ እንዲሁም
- ከመደበኛ በጀት ብር 5,522,539.55 እና ከውስጥ ገቢ ወጪ ብር 105,378.18፣ በድምሩ ብር **5,627,917.73** ከተፈቀደው በጀት በላይ ሥራ ላይ የዋለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

<u>መግለጫ</u>

በሂሳብ መደብ 6313 ባልተሠራበት በጀት የተያዘው ብር 12,906,944.98 በ09/10/2009 ለአሃዱ ኢንተርናሽናል የተከፈለ ብር 10,998,252.90፣ በ21/09/2009 ለጆሳንሳ ልጆች ኢትዮ ልማት የተከፈለ ብር 2,878,093.16፣ በ29/10/2009 ለሰልገን ትሬዲንግ የተከፈለ ብር 4,152,239.22 እና በ30/10/2009 ለኢታባ ኢንተርሜዲካል ኩባንያ የተከፈለ ብር 612,000.00፣ በድምሩ ብር 18,640,585.28 በ2009 በጀት ዓመት ለዕቃ አቅርቦት በቅድሚያ ክፍያ በሂሳብ መደብ 4253 የተከፈለውና ዕቃዎቹ በውሉ መሠረት ከበጀት ዓመቱ መጨረሻ በኋላ ገቢ የሚደረጉት ሥራ ላይ እንደዋለ በጀት ታስቦ ነው፡፡

4.2 <u>ስጋት</u>፣

- የበጀት ዝውውር ሣይደረግ ወይም ተጨማሪ በጀት ሳይፈቀድ ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀም መመሪያን ከመጣሱም ባሻገር የመንግሥትን ውስን ሀብት ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡
- የወጪ በጀቱ በእቅዱ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ የዩኒቨርሲቲውን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱ ትክክለኛነትን ላያመለክት ይችላል፡፡

4.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፣**

- ለወደፊቱ አሰራሩ እንዲስተካከል እና የዩኒቨርሲቲው ዕቅድና ክንውን የተጠጣመ እንዲሆን ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

የሥራ አመራሩ፣

- በጀት የተፈቀደው በየፕሮግራሙ ሲሆን በእያንዳዱ ፕሮግራም በጀት ላይ በሚታይበት ወቅት የተባለውን ያህል በጀት በስራ ላይ ሳይውል የቀረ የሚያሳይ በየፕሮግራሙ የቀሩት በአንድነት በሚደመርበት ወቅት የተባለው ያህል ቀሪ የሚያሳይ ቢሆንም ቀሪ በጀት ከተባለው ውስጥ ለእቃ አቅራቢዎች ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለው በወጪ መደብ ስለማያሳይ እንጂ በኮድ 6313 ላይ የተከፈለው ብቻ የታየው ያህል ሳይሆን ለእቃ አቅራቢዎች የቅድሚያ የተከፈለውንም የሚያጠቃልል መሆኑን፣
- ከበጀት በላይ የተከፈለው ክፍያ በወቅቱ የተማሪዎች የምግብ በጀትና በገበያው ሁኔታ ባለመጣጣሙ እንዲሁም ምግብ ሲያቀርብ የነበረው አቅራቢ አቅርቦቱን በማቋረጡ ምክንያት ለተማሪዎች ምግብ በኮሚቴ በለቀማ ግዥ በመፈፀሙ እንዲሁም የገበያው ሁኔታ በየጊዜው በመጨመሩ ምክንያት ይህ ችግር ሊገጥመን ችሏል፡፡ የቴሌኮምንኬሽን አገልግሎት የተፈቀደው በጀት በየወሩ ለአራቱ ካምፓስ የሚከፈለውን ያጣጣመ ካለመሆኑ የተነሣ የተፈፀመ ክፍያ ቢሆንም የበጀት አመቱ በመጠናቀቂያ ወቅት ክፍያ ቢል በመምጣቱ ተጨማሪም ሆነ የበጀት ዝውውር ለማድረግ ጊዜው በማለፍ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የተፈፀመ ክፍያ ሲሆን ለወደፊቱ የሚያስተካክሉ መሆኑን፣
- በጀት በአግባቡ ስራ ላይ አልዋለም የተባለው በነበረው የአከባቢ ፀጥታ ምክንያት ዩኒቨርሲቲው ተደጋጋሚ ጨረታ ቢያወጣ ተጫራቶች በበቂ ሁኔታ ባለመቅረባቸው እንዲሁም በጨረታው ቢያሸንፍም ቀርበው ውል ለመዋዋል ፍቃደኛ ባለመሆናቸው፣ በተጨማሪም በፕሮፎርማ ለመግዛትም ካለው የፀጥታ ችግር ምክንያት የእቃ ግዥ ሰራተኞች እንደልብ መንቀሳቀስ ባለመቻላቸው በበቂ ሁኔታ በስራ ላይ ሳይውል መቅረቱን እንዲሁም የግንባታ በነበረው የፀጥታ ችግር በወቅቱ የግንባታ ሰራተኞች ሥራቸውን ማከናወን ባለመቻላቸው ክፍያ ለመፈፀም ባለመቻሉ በጀቱ እንዲቀር መደረጉን በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

4.5 የኦዲተሩ አስተያየት፣

- በ6313 ላይ የተከፈለው ብቻ የታየው ያህል ሳይሆን ለእቃ አቅራቢዎች በቅድሚያ የተከፈለውንም የሚያጠቃልል መሆኑ ለተባለው በግኝቱ ሥራ እንደተጠቀሰው በሂሳብ መደብ 6313 ባልተሠራበት በጀት የተያዘው ብር 12,906,944.98 በ09/10/2009 ለአሃዱ ኢንተርናሽናል የተከፈለ ብር 10,998,252.90፣ በ21/09/2009 ለጃሳንሳ ልጆች ኢትዮ ልማት የተከፈለ ብር 2,878,093.16፣ በ29/10/2009 ለሰልገን ትሬዲንግ የተከፈለ ብር 4,152,239.22 እና በ30/10/2009 ለኢታባ ኢንተርሜዲካል ኩባንያ የተከፈለ ብር 612,000.00፣ በድምሩ ብር 18,640,585.28 በ2009 በጀት ዓመት ለዕቃ አቅርቦት በቅድሚያ ክፍያ በሂሳብ መደብ 4253 የተከፈለውና ዕቃዎቹ በውሉ መሠረት ከበጀት ዓመቱ መጨረሻ በኋላ ገቢ የሚደረጉት ሥራ ላይ እንደዋለ በጀት ታሳቢ ተደርጎ ነው፡፡
- ከበጀት በላይ የወጣውም እንደየአግባቡ ተጨማሪ በጀት በማስፈቀድ መይም በዝውውር ሊስተካከል ይገባ ነበር፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በማሻሻያ ሀሳቡ መሠረት መሥራት ያስፈልጋል፡፡

5. የንብረት አስተዳደር፣

5.1 አላቂና ቋሚ ዕቃዎች እንዲሁም ተሽከርካሪዎች፣

5.1.1 ግኝት

- በቁጥር ስምንት የሚሆኑ ዘመናዊ የወጥ እና የሻይ ማሽኖች /ድስቶች/ ወደ ዩኒቨርሲቲው ከገቡ ሶስት አመት ያህል ያስቆጠሩ ቢሆንም በኤሌትሪክ ኃይል እጥረት ምክንያት እስከ አሁን ድረስ አገልግሎት ሳይሰጡ ለዝገት እየተጋለጡ መሆኑ፣ ይህ በ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም አስተያየት ተሰጥቶበት የነበረ ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣
- በብዛት 179 የሚሆኑ 5450 DN Brother ሞዴል አዲስ ፕሪንተሮች ወደ የዩኒቨርሲቲው ከገቡ ከ5 ዓመት በላይ የሆናቸው ቢሆንም እስከ አሁን አገልግሎት ሳይሰጡ በእስቶር የተቀመጡ መሆኑ፤
- በበጀት ዓመቱ ዓመታዊ ቋሚ ንብረት ቆጠራ ያልተደረገ በመሆኑ፤

ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ

- አሮጌ እና አዲስ ጎዎች ሳይለያዩ በአንድ መጋዘን ውስጥ የተከማቹ መሆኑ፣

- አገልግሎት ካቆሙ ከሁለት አመት በላይ የሆናቸው እና መወገድ ያለባቸው በርካታ ጎማዎች እና የጎማ ካለመዳሪዎች ያልተወገዱ መሆኑ፤ ይህ በ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም አስተያየት ተሰጥቶበት የነበረ ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣
- አገልግሎት የማይሰጡ የሠሌዳ ቁጥር 4-05500 ኢት 1 ቶዮታ እንዲሁም 4-03971 ኢት እና 4-03973 ኢት፣ ሁለት መካከለኛ አውቶቡሶች መኖራቸው፣

ታውቋል።

5.1.2 ሥጋት

- የዩኒቨርሲቲው የንብረት አያያዝ፣ አመዘጋገብ እና አጠባበቅ በመመሪያው መሠረት ተፈፃሚ ካልሆነ ሁኔታው ንብረቶቹን ለከፋ ብልሽትና ብክነት ይዳርጋል፤ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍትም ይችላል።

5.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ

- ለበርካታ ጊዜ ያለ አገለልግሎት በየቦታው ወድቀው የሚገኙ ጎማዎች ትኩረት ተሰቷቸው ሊወገዱ ይገባል።
- ተሽከርካሪዎችን ጨምሮ ያለ አገልግሎት የተቀመጡ ንበረቶች ለብክነት እንዳይደረጉ በማስጠገን ወይም በማስወገድ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል።
- ጥቅም ላይ መዋል እየቻሉ ያልዋሉ ንብረቶች ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል።

5.1.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ፣

- ዘመናዊ የወጥ እና የሻይ ማሽኖች ቀደም ሲል አገልግሎት ያልሰጡት በኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት ቢሆንም አሁን ግን ችግሩ በከፊል ስለተፈታ አገልግሎት እንዲሰጥ የመገጣጠምና የመትከል ሥራ እየተሠራ መሆኑን፣
- ብዛት 179 የሚሆኑ 5450 DN Brother ሞዴል አዲስ ፕሪንተሮች ወደ ዩኒቨርሲቲው የገቡት ከ5 አመት በላይ ቢሆንም እርሱ እያለ ሌላ ተጨማሪ ያልተገዛ መሆኑን እና ነገር ግን ለተጠቃሚዎች በክፍላቸው እንደሌላቸው በማጣራት በማሰራጨት ላይ እንደሚገኙ እና ከግኝቱ በኋላ እንኳን በቁጥር 13 ለተጠቃሚዎች መስጠቱን

- በ2009 በጀት አመት አመታዊ የንብረት ቆጠራ ያልተደረገው ተቋሙ ሰፊ በመሆኑ፣ ያለው ንብረት ብዙ በመሆኑ እና ንብረት ክፍል በቂ የሰው ሀይል ስላልነበረው ያልተቆጠረ ሲሆን አሁን ግን ኮሚቴ ተዋቅሮ ሥራው መጀመሩን፣

<u>ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ</u>

- አሮጌ ጎማዎችና ባትሪዎች እንዲወገዱ በተለያዩ ጊዜ ለመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ ደብዳቤ ተጽፎ እስከ አሁን ያልተነሳ በመሆኑና ማከማቻ በማጣታችን በአንድ መጋዘን ውስጥ ቢቀመጡም መጋዘኑ ሁለት ቦታ ተከፍሎ አሮጌና አዲስ ሳይቀላቀል በጥንቃቄ የተቀመጠ ቢሆንም ችግሩ የመጋዘን እጥረት መሆኑን፣
- 4-05500 ከቆመ አንድ ዓመቱ እንደሆነና በቅርብ ቀን ተጠግኖ ወደ ሥራ የሚገባ እንደሚሆን፣
- 4-03971 እና 4-03973 በከባድ ብልሽት የቆመ ሲሆን በጫረታ አወዳድረው ለማሠራት ፕሮግራም የተያዘ መሆኑን፣
- በተደጋጋሚ ለመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት እንዲወገድ ደብደቤ ፅፈናል መተው ሊያስወግዱልን አልቻሉም፡፡ አሁንም ጥረቱን እንቀጥላለን፡፡ (የደብዳቤው አባሪ ከምላሹ ጋር ተያይዞ ቀርቧል)

6. <u>ሌሎች ጉዳዮች፣</u>

6.1 <u>የውስጥ ኦዲትን በተመለከተ፣</u>

6.1.1 <u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 አንቀጽ 8/2 የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል ተገቢው የሙያ ብቃት፤ ዕውቀትና ክህሎት በላቸው ባለሙያዎች መደራጀት እንዳለበት ይገልፃል፡፡

በዚህ መሠረት የዩኒቨርሲቲው የውስጥ ኦዲት የሰው ኃይልን በተመለከተ ቅኝት ሲደረግ በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ኦዲት የሰው ኃይል መዋቅር መሠረት ለክፍሉ 14 የኦዲት ባለሙያዎች የሚያስፈልግ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት 2 የኦዲት ባለሙያዎች ብቻ ያሉት በመሆኑ ክፍሉ በባለሙያዎች ያልተሟላ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

6.1.2 <u>ሥጋት</u>

- የውስጥ ኦዲት ክፍሉ በበቂ የሰው ኃይል ካልተደራጀ በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት አተገባበር ላይ የሚደረገው ክትትል በቂ ላይሆን ይችላል፡፡

6.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ

- ክፍሉ አግባብነት ባለው የሰው ኃይል በቅጥር፣ በደረጃ ዕድገት፣ ወይም በዝውውር እንዲሟላ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

6.1.4 የሥራ አመራሩ ምለሽ፤

የሥራ አመራሩ ዩኒቨርሲቲው መዋቅር ሰርቶ ከሀምሌ 01 ቀን 2009 ጀምሮ ተግባራዊ ማድረጉን፣ በዚህ መሰረት ማስታወቂያ ሳይወጣ የውስጥ ሰራተኞች መደልደል ስላለበት እስከ ታህሳስ 25 ቀን 2010 መቆየቱን እና በቀጣይ በተፈቀደላቸው መዋቅር መሰረት ማስታወቂያ አውጥተው የሚቀጥሩ እንደሆነ በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡

7. እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች፣

7.1 ግኝት፣

- በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2(በ) መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በውጭ ኦዲት ወይም በውስጥ ኦዲት ሪፖርት በተመለከተው መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡
- በተጨማሪም የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምስት አንቀጽ 17/3 መሰርት ተመርማሪ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ እንዳለባቸውና እርምጃ ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፈዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡

ይሁን እንጂ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የአምቦ ዩኒቨርስቲ የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ውስጥ፣

- ዩኒቨርሲቲው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስተር ሳያስፈቅድ በተማሪዎች ህብረት ስም በተከፈተ ከኢትዮጵ ንግድ ባንክ አምቦ ቅርንጫፍ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000015171786 ከቤቶች ኪራይ፤ ከጀበና ቡና አገልግሎት እና ከፑልና ጁቶኒ አገልግሎት የሚያገኛቸውን ገቢ በራሱ በከፈተ የሂሳብ ቁጥር ገቢ የሚያደርግ መሆኑ፤

- ዩኒቨርሲቲው መዝናና ክበብ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝና ገንዘብ ወጪ ማዘዣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ አምቦ ኮሌጅ የተማሪዎች ማዝናኛ ክበብ ስም በታተመው ክፍያ ቨውቸሮች የሚሰራ መሆኑ፤
- የኒቨርሲቲው 27 ከሚሆኑ የስራ ተቋራጮች በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ሰርቶ ላላስረከቡና ዩኒቨርሲቲውን ላስተጓጎሉበት በድምሩ የብር 8,527,962.55 የጉዳት ካሳ ለመንግስት ገቢ መደረግ ሲገባዉ ያልተደረገ መሆኑን፤
- ዩኒቨርሲቲው በተለያዩ ቀናት የ2ኛ እድገትና ትራንስፎርመሽን እቅድ ላዘጋጁበት ብር 18,000.00፤ ከአምቦ ጉደር አስፓልት ዳር የችግን ተከላ አስፈላጊውን ስራ ላከናወኑ ለአስራ አንድ ኮሚቴ አባላት በድምሩ 41,000.00፤ ለካይዘን ስራ ትግበራ የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ የካይዘን ልማት ቡድን አባላት ልዩ ትኩረት ላሳዩ በድምሩ ብር 112,300.00፤ የሪፈራል ሆስፒታል መንገድ በውጪ በኩል ከዋናው አስፓልት መንገድ ጋር የማገናኘት ስራ ላስተባበሩበት ለአስራ ሶስት ኮሚቴ አባላት በድምሩ 34,700.00 ማበረታቻ በሚል አላግባብ ክፍ የተፈጸመ፤
- ዩኒቨርሲቲው በቀን 30/01/08 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 21738 ብር 81,980.73 ወጪ በማድረግ ማገርና ቋሚ እንጨት ግዥ በመፈጸም ለተለያዩ ግለሰቦች ክፍያ ሲፈጽም ስለ ተከፋይ ተቀናሽ ታክስ መቀነስ የነበረበት ብር 17,278.80 ያልተቀነሰ መሆኑ፤
- በኬሚካል ግምጃ ቤት ውስጥ በግዥና በእርዳታ የተገኙ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ የተለያዩ የኬሚስተሪ መሳሪያዎች እና የተለያዩ ኬሚካሎች ያለአገልግሎት ለብዙ ዓመታት የተቀመጡ መሆናቸውና የመጠቀሚያ ጊዜቸው ያለፈባቸው ኬሚካሎች ሳይወገዱ ለበርካታ ጊዜ የተቀመጡ መሆናቸው፤

<u>የ2007 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝትን በተመለከተ</u>

- የቱሉ ኮርማ የሀገር በቀል ዛፎች ማዕከል ሚያዚያ 26/2007 በተደረገው የርክክብ ስነ ስርዓት ያማረና የደመቀ እንዲሆን ላደረጉ ኮሚቴ አባላት ማበረታቻ እንዲከፈል የዩኒቨርሲቲው ማነጅመንት በሰጠው ውሳኔ መሰረት ብር 73,395.00 አላግባብ የተከፈለው ክፍያ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

  በሚሉ ግኝቶች ላይ እስከ 2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ማብቂያ ጊዜ ድረስ እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ ታውቋል።

7.2 ስጋት፣

በኦዲት ግኝቶች ላይ አፋጣኝ የእርምት እርምጃ አለመውሰድ፡-

- ከፍተኛ ገንዘብና ጊዜን ለኪሳራ ሊዳርግ የሚችል ነው፡፡
- ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋትና መጉደል መንገድ የሚከፍት አሠራር በመሆኑ ተጠያቂነትንም ሊያስከትል ይችላል፡፡
- በሕግ፤ በደንብና መመሪያ ላይ በመመስረት የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶችን ሥራ ላይ አለማዋል የተሻለ አሠራርን መከተል አያስችልም፡፡

7.3 የማሻሻያ ሃሳብ፤

- የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከፍተኛ ገንዘብና ጊዜ የወጣባቸው በመሆኑ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድባቸው የሥራ አመራሩ፣ የዩኒቨርስቲው ቦርድና የሚመለከታቸው የበላይ ኃላፊዎች ለጉዳዩ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

7.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

የሥራ አመራሩ፣

የ2008 በጀት ዓመትን በተመለከተ

- ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የባንክ ሂሣብ ለመክፍት ፍቃድ የሚሰጠው ሪፖርቱ የሚቀርበው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ለሆነ የዩኒቨርሲቲ ሂሳብ ከሆነ ብቻ እንጂ በተማሪዎች ህብረት ስም ባንክ መክፈት እንደማይቻል፣ ነገር ግን የባንክ አካውንት መክፈት ካለበትም በዩኒቨርስቲው ፕሬዚዳንት በኩል ተፈቅዶ መከፈት እንዳለበት እንደተገለጸላቸው፣ አሁንም የተማሪዎች ህብረት የሚጠቀሙበት አካውንት በዩኒቨርሲቲው ፕረዘዳንት እውቅና የተከፈተ ሲሆን ስሙም የአምቦ ኮሌጅ ተማሪዎች መዝናገኛ ክበብ መሆኑን፣
- የመዝናኛ ክበቡም የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ እና የገንዘብ ወጪ ማዘዣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ አምቦ ኮሌጅ በሚለው የቆየ ቫውቸር መጠቀም ስህተት ስለተባለ ሌላ ደረሰኝ ለማሳተም ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ደረሰኝ በአምቦ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ህብረት ስም እንድናሳትም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ደብዳቤ በመፃፍ እንዲፈቀድላቸው ብንጠይቁም ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ገንዘቡ የሚሰበሰበው የዩኒቨርሲቲው ከሆነ እንጂ ለተማሪዎች ህብረት እራሱን የቻለ ስለሆነ በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በኩል

ታይቶ ሊታተም ይችላል ስለተባሉ የታተመውን ደረሰኝ በዚሁ መሠረት የታተመ በመሆኑ እየተጠቀሙበት መሆኑን፤

- የጉዳት ካሳን በተመለከተ፡-
  - በዩኒቨርሲቲዉ ዉስጥ የግንባታ ስራ ሲያከናዉኑ የነበሩ ተቋራጮች በአብዛኛዉ መንግሥት ባስቀመጠዉ አቅጣጫ መሰረት አቅማቸዉን ለማጎልበት ሲባል በወቅቱ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ተመርጠዉ ያለጨረታ ስራዉ በቁርጥ ዋጋ የተሰጣቸዉ በመሆኑ በየጊዜዉ የሚከሰተዉ የገበያ ዋጋ ጭማሪ የኮንትራክተሮቹን አቅም የተፈታተነ በመሆኑ በሚፈለገዉ ጊዜ ዉስጥ ስራዉን ማጠናቀቅ እንዳይችሉ እንዳደረጋቸው፣
  - ለግንባታ የሚውሉ ግብአቶች (ሲሚንቶና ብረት የመሳሰሉ) በት/ሚ/ር በኩል ተገዝተዉ ሲቀርቡ የነበረ ሲሆን አልፎ አልፎ በሚፈጠረዉ እጥረትና የግዥ ሂደት መጓተት ጋር ተያይዞ መዘግየቶች ስለነበሩ፣
  - በወቅቱ የስራ ዕድል ለመፍጠር ሲባል እንደ ብሎኬት፣ የኮንክሪት እና ፕሪከስት ማቴሪያሎች አቅርቦት ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የተሰጠ በመሆኑ እነዚህን ግብዓቶች በሚፈለገዉ ጊዜና መጠን በማቅረብ ላይ ከፍተኛ ችግር ስለነበረ፣
  - የአካባቢው አፈር ዓይነት ጥቁር /ኮትቻ/ በመሆኑ በዝናብ ወቅት ለግንባታ ስለሚያስቸግር ስራዎቹ ለረጅም ወራት ሲቋረጡ ስለነበረ፣
  - በፀጥታ ችግር ምክንያት በተለያዩ ጊዜያት ኮንትራክተሮች ስራ ለማቋረጥ ሲገደዱ ስለነበ፣ረ
  - ከወሰን ማስከበር ጋር ተያይዞ የተፈጠረ መዘግየት፣
  - የመሠረተ ልማት ግብዓቶች በወቅቱ ያለማሟላት ችግር (ለምሳሌ የዉሃና ኤሌክትሪክ አገልግሎት በሚፈለገዉ ጊዜ አለመቅረብ)
  - የአዋሮ ግቢ (ቴክኖሎጂ ተቋም) አዲስ ከመሆኑ አንፃር የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዳይስተጓጎል ኮንትራክተሮች ሥራውን አጠናቀው የርክክብ ሂደቱ ሳይፈጸም ህንፃዎች አገልግሎት እንዲሰጡ ሲደረግ ስለነበረ ኮንትራክተሩ በወቅቱ የመጀመሪያ ርክክብ ሳያደርግ የተሰሩ ሥራዎች በተማሪዎች ስለሚበላሹ በሚፈጠሩ ክፍተቶች የርክክብ ጊዜ መራዘም፣
  - ከዲዛይን ክለሳ ምክኒያት የጊዜ መባከን፣

ምክኒያቶች በተቋራጮቹ ላይ እርምጃ ቢወሰድ ሥራዉ ሙሉ በሙሉ ሊቋረጥ ስለሚችል በመነጋገር ስራዉን እንዲያጠናቅቁ መደረጉን፣

- በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በተለያዩ የሥራ መስክ በኮሚቴነት ተመርጠው ለሰሩ መምህራንና ሠራተኞች የማበረታቻ ክፍያ የተከፈላቸው ከመደበኛ ሥራቸው ጋር የማይገናኝ ሥራን በቡድን በመሆን፣ ከሥራ ሰዓት ውጪ ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ በትርፍ ሰዓታቸው ስለሰሩ የተከፈሉ ክፍያዎች መሆናቸውን እና እነኚህ ክፍያዎች ከጥቅማ ጥቅም ወይም ከትርፍ ሰዓት ሥራ ጋር የማይገናኙ ስለሆኑ በማኔጅመንት ሲታመንበትና የሰሩት ሥራ ተመዝኖ ቃለ-ጉባዔዎች እየተያዘ የተከፈለ የማትጊያ/ማበረታቻ ክፍያዎች እንደነበሩ፣ በሌላ በኩል የካይዘን አሰራር ማበረታቻን የሚደግፍ በመሆኑና ሌሎች ሰራተኞች የተሻለና ከሚጠበቅባቸው በላይ እንዲሰሩ ለማድረግ እንደሆነ፣ ሆኖም ግን እንደዚህ ዓይነት ክፍያዎችን በተሰጠው የማሻሻያ አስተየየት መሰረት ከዝያ ጊዜ በኋላ ማቆማቸውን፣
- የማገር እና ቋሚ እንጨቶች ግዥው ከአምቦ ከተማ በሚገዘበት ወቅት ተጨማሪ የዋጋ ማቅረቢያ ማግኘት ባለመቻሉ እና አዲስ አበባ ሄዶ ተጨማሪ የዋጋ ማቅረቢያ ለመሰብሰብ ከግዥው አስቸኳይነት የተነሳ የተከሰተ ስለሆነና በተጨማሪም በግዥ ሰራተኞች አማካኝነት ከተለያዩ ግለሰቦች የተገዙት ማገር እና ቋሚ እንጨቶች ለመግዛት በአካባቢያቸው ያሉት የእንጨት ነጋዴዎች ንግድ ፈቃድ ስለሌላቸው ከገበሬዎች ላይ ለመግዛት የተገደዱ ሲሆን በሚገዛበት ወቅት 2% እየቆረጡ የገዙ ሲሆን ነገር ግን 30% ቢቆረጥባቸው እንጨቱን ለመሸጥ ፍቃደኛ ባለመሆናቸው እንዲሁም ለነገጋዴዎች ምንም ሳይቆረጥብን መሸጥ እንችላለን ስለሚሏቸው ካለባቸው ችግር የተነሳ ለመግዛት የተገደዱ መሆኑን ገልጸው የኦዲት አስተያየት ከተሰጣቸው በኋላ እንደዚህ አይነት ግዥዎችን ያቆሙ መሆኑን፣
- የሚወገዱ ኬሚካሎችን በተመለከተ በተደጋጋሚ ለመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት እንዲወገድ ደብደቤ መጻፋቸውን፣ ነገር ግን እስከ ዛሬ ሊያስወግዱላቸው አለመቻላቸውን እና አሁንም ጥረቱን እንደሚቀጥሉ፣

<u>**የ2007 በጀት ዓመትን በተመለከተ**</u>

- በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በኮሚቴነት ተመርጠው ለሰሩ ሠራተኞች የማበረታቻ ክፍያ የተከፈላቸው ከመደበኛ ሥራቸው ጋር የማይገናኝ ሥራን ከሥራ ሰዓት ውጪ ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ በትርፍ ሰዓታቸው ቱሉ ኮርማ ኤጄሬ ወረዳ ድረስ በመሄድ (ከ70 ኪሎ ሜትር በላይ) **ያለ ዉሎ አበል** ስለሰሩ የተከፈለ ክፍያ መሆኑን እና ይህ ክፍያ ከጥቅማ

ጥቅም ወይም ከትርፍ ሰዓት ሥራ ጋር የማይገናኝ ስለሆነ በማኔጅመንት ሲታመንበትና የሰሩት ሥራ ተመዝኖ ቃለ-ጉባኤ እየተያዘ እንደ ዉሎ አበል የተከፈለ የማትጊያ/ማበረታቻ ክፍያ እንደነበር፣ ሆኖም ግን እንደዚህ ዓይነት የዉሎ አበል ክፍያዎችን በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት ከዚያ ጊዜ ወዲህ ማቆማቸውን፣ ለሥራ አመራር ደብዳቤ በላኩት ምላሽ ገለረጸዋል፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የስራ ትብብር እናመሰግናለን!

አባሪ ቁጥር 1

ተ.ቁ	የትምህርት ማዕረግ	የተከፈለበት ተመን	የተቀባይ ብዛት	ድምር
1	Asst. Lecturer	1,680.00	1	1,680.00
2	Lecturer	7,916.30	1	7,916.30
3	Lecturer	2,160.00	4	8,640.00
4	Lecturer	4,416.00	1	4,416.00
5	Lecturer	8,540.30	1	8,540.30
6	Lecturer	4,320.00	1	4,320.00
7	GA II	2,115.25	1	2,115.25
8	Lecturer	288.00	7	2,016.00
9	Lecturer	6,696.00	2	13,392.00
10	GA II	5,443.30	1	5,443.30
11	TA	1,800.00	1	1,800.00
12	Lecturer	3,264.00	1	3,264.00
13	Lecturer	2,928.00	1	2,928.00
14	Asst .Professor	8,507.05	2	17,014.10
15	Lecturer	1,440.00	3	4,320.00
16	Lecturer	3,600.00	2	7,200.00
17	Lecturer	720.00	2	1,440.00
18	Lab Attendant	360.00	1	360.00
19	Lecturer	4,399.80	1	4,399.80
20	Asst. Lecturer	1,120.00	1	1,120.00
21	Lecturer	6,092.30	2	12,184.60
22	TAI	480.00	1	480.00
23	Lecturer	2,040.00	1	2,040.00
24	Lecturer	9,260.30	1	9,260.30
25	Lecturer	5,959.80	1	5,959.80
26	Lecturer	6,360.00	1	6,360.00
27	Lecturer	5,420.30	1	5,420.30
28	Lecturer	6,380.30	2	12,760.60
29	GA II	4,923.30	1	4,923.30
30	Lecturer	4,560.00	1	4,560.00
31	Lecturer	3,199.80	1	3,199.80
32	Asst. Lecturer	10,239.50	1	10,239.50
33	Lecturer	10,796.30	1	10,796.30

34	Lecturer	3,480.00	1	3,480.00
35	TAI	960.00	1	960.00
36	Lecturer	3,840.00	1	3,840.00
37	Lecturer	4,080.00	1	4,080.00
38	Lecturer	15,936.00	1	15,936.00
39	Lecturer	7,820.30	1	7,820.30
40	Asst .Professor	6,272.00	1	6,272.00
41	Asst .Professor	8,123.05	1	8,123.05
42	Lecturer	5,040.00	1	5,040.00
				246,060.90

አባሪ ቁጥር 2

ተ.ቁ	የትምህርት ማዕረግ	የተከፈለበት ተመን	የተቀባይ ብዛት	ድምር
1	Lecturer	34,560.00	1	34,560.00
2	Lecturer	23,040.00	3	69,120.00
3	Lecturer	14,976.00	1	14,976.00
4	Lecturer	14,400.00	1	14,400.00
5	Asst.Lecturer	8,960.00	1	8,960.00
6	Lecturer	7,680.00	1	7,680.00
7	Asst. Lecturer	5,973.10	1	5,973.10
				ድምር 155,669.10

አባሪ ቁጥር 3

ተ.ቁ	የተከፈለበት ተመን	የተቀባይ ብዛት	ድምር
1	60	12	720.00
2	90	74	6,660.00
3	120	45	5,400.00
4	150	17	2,550.00
5	200	17	3,400.00
6	225	6	1,350.00
7	300	23	6,900.00

8	375	24	9,000.00
9	400	1	400.00
10	450	1	450.00
11	525	2	1,050.00
12	750	5	3,750.00
13	675	1	675.00
13	900	1	900.00
		ድምር	**43,205**

አባሪ ቁጥር 4

ተ.ቁ	የተከፈለበት ሰው ብዛት	ሴሽን	የክፍያ ተመን	ድምር
1	8	1	2,500.00	20,000.00
2	9	2	2,500.00	45,000.00
3	13	3	2,500.00	97,500.00
4	9	4	2,500.00	90,000.00
5	6	5	2,500.00	75,000.00
6	1	6	2,500.00	15,000.00
			ድምር	342,500.00

አባሪ ቁጥር 5

የድህረ ምረቃ የውጭ ፈታኞች ክፍያ				
1	9	1	2,500.00	22,500.00
2	16	2	2,500.00	80,000.00
3	4	3	2,500.00	30,000.00
4	4	4	2,500.00	40,000.00
5	2	5	2,500.00	25,000.00
6	2	6	2,500.00	30,000.00
7	1	7	2,500.00	17,500.00
8	1	8	2,500.00	20,000.00
			ድምር	**265,000.00**
የድህረ ምረቃ ዋና አማካሪዎች ክፍያ				
9	16	1	3,500.00	56,000.00
10	8	2	3,500.00	56,000.00
11	4	3	3,500.00	42,000.00
12	5	4	3,500.00	70,000.00

13	2	6	3,500.00	42,000.00
14	1	11	3,500.00	38,500.00
			ድምር	**304,500.00**
ለሲቀ መናብርት				
15	7	1	500.00	3,500.00
16	11	2	500.00	11,000.00
17	12	3	500.00	18,000.00
18	3	4	500.00	6,000.00
19	3	5	500.00	7,500.00
20	1	6	500.00	3,000.00
21	1	10	500.00	5,000.00
22	1	11	500.00	5,500.00
			ድምር	**59,500.00**

አባሪ ቁጥር 6 (ተሰብሳቢ 4201)

ተ.ቁ	የገንዘቡ ልክ	ገንዘቡ የሚፈለግበት ድርጅት/ግለሰብ	በተሰብሳቢ የተያዘበት ቀን
1	6,323.59	ት/ሚንስተር	
2	855.00	ደሳለኝ ወልዴ	30/10/2006
3	7,600.00	በየነ ሩዳ	30/10/2005
4	700.00	ሃብታሙ ምትኩ	30/10/2004
5	3,000.00	ጫላ ባይሳ	30/10/2007
6	777.00	ፀጋ ግርማ	30/10/2007
7	772.00	ታሪኩ ተሾመ	30/10/2008
8	772.00	ታደሰ ጫላ	30/10/2007
9	2,200.00	አብረሃም መንገሻ	30/10/2008
10	3,600.00	ተወልደ ብርሀን ሀይሉ	30/10/2008
11	3,600.00	ወርቂ አንለይ	30/10/2008
	30,199.59		

አባሪ ቁጥር 7 (ተሰብሳቢ 4253)

ተ.ቁ	የገንዘቡ ልክ	የአቅራቢው ድርጅት ሥም	በተሰበወሳቢ የተመዘገበበት ቀን
1	584,899.49	ሙሉግታ ጣሰው	18-10-06
2	4,165,968.00	ሲመን ቢዚነስ ሬዲንግ	12-02-07
3	2,435,688.00	ሜዲካል ፌንድ ሳፕላይስ የሂኪምና ዕቃ አቅራቢ	24-10-08
4	15,750,000.00	የመንግሥት ግዥ ለመጽኃፍ ግዥ	30-10-08
ድምር	22,936,555.49		